# ቀጣይ "ምርጫ" እና ቀጣይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች አካሄድ፤ አንድ እይታ፡ አስራ አንድ አስተያየቶች

**ተክለሚካኤል አበበ**

**ከምርጫ 2010 ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ውይይት የቀረበ የመነሻ ሀሳብ**

**ቫንኩቨር ካናዳ**

Saturday, December 13, 2008-12-13

በ2010ም ይሁን ከዚህ በኋላ፡ መቼም ምርጫ ከተካሄደ፡ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በኢህአዴግ መንግስትነት በሚካሄድ ማናቸውም ምርጫ መሳተፍ ይገባቸዋልን የሚለውን ጥያቄ፡ "አዎ መሳተፍ አለባቸው" ብቻ ሳይሆን "ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መሳተፍ፡ መግባት አለባቸው" ማለቴ ብዙዎቻችሁን ሳያስገርም፡ ምናልባትም ይሄ ሰው ምን ነካው? ጤነኛም አይደል እንዴ ሳያሰኛችሁ አይቀርም። ይሄንን፡ ያልኩትን፡ ያልኩበትን ምክንያት ከመዘርዘሬ በፊት፡ ለማነሳቸው ዋና ዋና ነጥቦቼ ግንዛቤ እንዲያስጨብጡልኝና፡ የአድማጮቼን ምናብ ለመሰብሰብ አንድ ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን አስቀድሜ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁኝ።

አንደኛ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ፡ ሕወሀት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ግዜ ጀምሮ፡ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ አድረጓል፡ ወደፊትም ያደርጋል፡ በኢትዮጵያ ውስጥም ነጻ ምርጫን ሊያስተማምኑ የሚችሉ ነጻና ገለልተኛ ተቋማት ማለትም ነጻ ምርጫ ቦርድ ወይንም ነጻ ፍርድቤት፡ አሉ ብዬ አላምንም። አሁን ባለው ሁኔታ፡ ነገሮችን ወደፊት ካላሻሻለ በስተቀር፡ ነጻና ተወዳድረን የምናሸንፍበት ወይም የምንሸነፍበት የምርጫ ስርአት የለም። ዋናው ትግልም እነዚህን ነጻ ተቋማት መፍጠሩ ነው። ስለዚህ ተቃዋሚዎች ወደ ምርጫ መግባት አለባቸው ስል፡ በሰፊው ዴሞክራሲን ለማምጣት፡ በጠባቡ እነዚህን ነጻ ተቋማት ለመፍጠር በምናደርገው ትግል የተቃዋሚዎች ነጻ እንዳልሆኑ በምናምናቸውም ተቋማት ውስጥ መታገል አስፈላጊ ነው ብዬ ስለማምንና፡ በሌሎችም ዝቅ ብዬ በምጠቅሳቸው ምክንያቶች እንጂ፡ ነጻ ምርጫን ተስፋ ከማድረግ በመነጨ ምክንያት አይደለም።

ሁለተኛ፡ ተቃዋሚዎች ወደምርጫ "ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መግባት አለባቸው" ስል፡ አሁን ያለውን የምርጫ ህግና ጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታ መልካም እንደሆነ ተቀብለው፡ በእኩልነት እንደሚወዳደሩ አምነው፡ ምንም ቅድመ ሁኔታዎችን ሳያስቀምጡ ይግቡ ማለቴ ሳይሆን፤ ትክክለኛና ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግ መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች ያስቀምጡ፤ በምንም መልኩ ግን አስቀድመው እነዚህ የምናስቀምጣቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ካልተስተካከሉ ወደ ምርጫ አንገባም የሚል መደራደሪያ አያስቀምጡ ለማለት ነው። በሌላ አነጋገር። ወደ ምርጫ እንገባለን፡ ወደምርጫ የምነገባው ግን ምርጫው ፍትሀዊ ይሆናል፡ ነጻ የምርጫ ቦርድ አለ፡ ብንበደል የምንከስበትና ፍትህ የሚሰጠን የምንተማመንበት ነጻ ፍርድ ቤት አለ ብለን ሳይሆን፡ እነሱ

የሉም ብለን፡ እነሱም አለመነኖራቸውን ለአለም ለማሳየትና፡ እነሱ በሌሉበት ሁኔታ ውስጥም ይሄንን ስርአት ለማሸነፍ አንቦዝንም ብለው ነው፡ ብለው ይግቡ ለማለት ነው።

ሶስተኛ ሰዎች የሚያዋጣቸውን የትግል መንገድ የመምረጥ፡ ህዝብም ያንን የትግል ስልት መከተል ወይም አለመከተል መብት አለው፡ ይሄ ተቃዋሚዎች የሚከተሉትን መንገድ ካልወደደውም፡ ራሱ ህዝቡ ሊያስተምራቸው፡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መልስ ሊሰጣቸው ይችላል የሚለው ግምቴም ይታወቅልኝ። ይሄንንም ትንሽ ልሞርደውና፡ በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ ስርአቱን የሚረዳ ወይም የሚያግዝ ወይንም የሚደግፍ ስራ እስካልሰሩ ድረስ፡ ተቃዋሚዎች የመሰላቸውን የትግል መንገድ የመምረጥ መብታቸው የተጠበቀ ነው ከሚል ግምት ተነስቼ ነው። የዚህ ተቃራኒውና ግልባጩ፡ ምንድነው እሱ፡ ተቃዋሚዎች ወይም ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ ኢህአዴግን ለመጣል የሚታገል ሀይል መከተል ያለበት ወይም ያለባቸው መንገድ አንድ ብቻ ነው ያልን እለት፡ በምርጫ የማናምን፡ ሌላ ኢህአዴግን እንሆናለን። ያደግሞ እንዲወገድ የምንፈልገውን ችግር እኛም ደገምነው ማለት ነው።

እነዚህን ብዬ፡ የሚቀጥሉትን ደግሞ እላለሁ። ወደ አንደኛው ነጥቤ ላምራ። በዚህ ሰዓት እንደኔ አስተያየት፡ ከምርጫ ጋር በተያያዘ፡ ኬንያን እያየ፡ ዙምባቤን እያየ፡ ራሷን ኢትዮጵያን እያየ፡ የኢህአዴግ ትልቁና ዋንኛው ጸሎቱ፡ ተቃዋሚዎች ወደምርጫ እንገባም እንዲሉና እንዳይገቡበት ነው። በምንም መልኩ እንደ 2005ቱ ምርጫ የሚያሳጣውና የሚፈታተነው ተወዳዳሪ ፓርቲ እንዳይኖር ለማድረግ የማይሳለው ስለት አይኖርም። ተቃዋሚዎች ወደ ምርጫ ቢገቡ፡ ለኢህአዴግ ራስ ምታት ነው። ታዛቢዎች ሊመጡ ነው። መገናኛ ብዙሀንን ሊለቅ ነው። ሊሳጣና ሊተች ነው። በረሀብና በኑሮ ውድነት የተማረረው ህዝብ በሱ ላይ አሁንም በድጋሚ እንዲነሳሳና እንዲያመጽ የሚቀሰቅስ መድረክ እንዲፈቅድ ሊገደድ ነው። ሙስና ሊጋለጥ ነው። ስለዚህ፡ የተቃዋሚዎችን ወደ ምርጫ መግባት ከምንም በላይ የማይፈልገው ራሱ ኢህአዴግ ነው። ስለዚህ ተቃዋሚዎች ወደምርጫ አንገባም ቢሉ አትራፊው ኢህአዴግ ነው። ያንን በማለታቸው ተቃዋሚዎችም ይሁን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያተርፉት ምንም ነገር የለም ብቻ ሳይሆን ይጎዳሉም።

ወደምርጫ መግባት ለተቃዋሚዎች ትልቅ ሀይልን ብርታትንና አሁን ያጡትን መድረክ ይሰጣቸዋል። በርግጥ ይሄንን ያልኩት ወይም የምለው፡ ተቃዋሚዎች ወደምርጫ ቢገቡ፡ ኢህአዴግ በይሉኝታም ይሁን በግድ ለተቃዋሚዎች ትንሽም ብትሆን፡ የመንቀሻቀሻ የመናገሪያ የመከራከሪያ መድረክ ይሰጣቸዋል ብዬ በመገመት ነው። ስለዚህ ኢህአዴግ የለም ምንም መድረክ አልሰጥም ካለ፡ ይሄ የጠቀስኩት ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ላያስኬድ ይችላል። ከሆነና ተቃዋሚዎችና ኢህአዴግ ፊት ለፊት በህዝባዊ መድረኮች ወይም በመገናኛ መድረክ ላይ ከተቀመጡ፡ ኢህአዴግን ሙስና፡ የኢህአዴግን ሰው ሰራሽ ረሀብ፡ የኢህአዴግን ሰው-ሰራሽ ሽብር ለማጋለጥና ኢህአዴግ ላይ ለማላገጥ፡ ምርጫ ባይገቡ የማያገኙትን መድረክን ያገኛሉ።

ዞረ ዞሮ፡ ተቃዋሚዎች ምርጫ ባለመግባታቸው፡ የገቡትም ከምርጫ በመውጣታቸው፡ ኢህአዴግ ምርጫ ከማድረግ ወደኋላ አይልም። ባለፈው ሚያዚያ ያደረገውን ወደ 3.5 ሚሊዮን የሚጠጉ ተወዳዳሪዎችን ያሳተፈበትን የቀበሌና የወረዳ ምርጫ ልብ ይሏል። ምርጫውም ተደረገ፡ ኢህአዴግም ይገዛል፡ እኛም የፈየድነው ምንም ነገር የለም። እንደውም ይባስ ብሎ፡ ሶስት ሚሊዮን ተወዳዳሪዎች አቅርቦ አረፈው። በዘጠና ዘጠኝ ከሙቶው መሰለኝ ያሸነፈው። ተቃዋሚዎች፡ ምርጫ ቢገቡም ባይገቡም ኢህአዴግ ምርጫውን ያደርጋል። ምናልባት ከፓርላማ ምርጫ ጋር ሲወዳደር፡ የወረዳና የቀበሌ ምርጫ ብዙ ቦታ ላይሰጠው ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ፡ በላፈው ሚያዚአ በተደረገው የኢህአዴግ ምርጫ ተቃዋሚዎች ላለመሳተፋቸው አጥጋቢ ምክንያት ቢኖርም፡ ከዚያ ተቃዋሚዎች ካልተሳተፉበት ምርጫ ይልቅ ተቃዋሚዎች የተሳተፉበት ምርጫ ነው ከፍተኛውን የህዝብ ስሜት የቀሰቀሰ፡ የአለምን ምላሽ የቀሰቀሰ፡ የእኛ በውጭ የምንገኘውንም ኢትዮጵያዊያን ለተወሰነ ግዜም ቢሆን በከፍተኛ ሁኔታ ያንቀሳቀሰ። ስለዚህ በምርጫው ባለመሳተፍ የምናገኘው ምላሽ በምርጫ መሳተፍ ከምናገኘው ምላሽ ወይም ተነሳሽነት ላቀ ነው የሚል ማስረጃ ካልቀረበ መስተቀር፡ በምርጫ መሳተፉ፡ በምርጫ ካለመሳተፉ የበለጠ ውጤታማ ነው።

በዲሞክራሲያዊም ይሁን ዴሞክራሲያዊ ባልሆኑ አገሮች ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን ብንመለከት (ካናዳን፡ ኬንያን፡ አሜሪካንን፡ ጋናን ራሷን ኢትዮጵያን ይመለከቷል)፡ ገንዘብ በማዋጣት፡ አባላትን በማደራጀት፡ ቅስቀሳን በማስፋት ረገድ ተቃዋሚዎች በከፍተኛ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱት፡ የምርጫ ሰሞን ነው። ያለፈውን የኢትዮጵያን ምርጫ ብንመለከት፡ ተቃዋሚ ድርጅቶች አብዛኛውን ሀይላቸውንና ገንዘባቸውን እንዲሁም ድርጅቶቻቸውን የማቀናጀት፡ ግንባር የመፍጠር ስራ ላይ የተሰማሩት፡ በምርጫው ሰሞን አስቀድሞ ባሉ ጥቂት ወራት ውስጥ ነው። ምርጫ ካለና ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን

ካንቀሳቀሳቸው አባላትን ለመመልመል፡ ገንዘብ ለማሰባሰብ፡ ግንባር ለመፍጠር፡ ስርአቱን ለማሳጣት፡ ከህዝብ ጋር ለመገናኘት ትክክለኛውና ወርቃማው አጋጣሚ ምርጫ ነው። ተቃዋሚዎች ምርጫ ውስጥ ካልገቡ፡ ምንም አይነት ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበት እድልም ሰበብም አይኖርም። በሰላማዊ መንገድ እዚያው አገር ቤት እንታገላለን ብለው የሚንቀሳቀሱትን ድርጅቶች ማለቴ ነው። ከዚያ መለስ እንታገላለን የሚሉ ወይም የምንል፡ አገር ቤት ካሉት ድርጅቶች ጋር የማያገናኝና እኛው እዚሁ ልንወጣው የሚገን የቤት ስራ ስላለን፡ ይሄ ጽሁፍ እኛን አይመለከትም።

ይሄን ካነሳሁ አይቀር ግን፡ ይሄ ተቃዋሚዎች ምርጫ ውስጥ መግባት አለባቸው ማለት ሌላ የትግል መስክ አያስፈልግም ማለት እናዳልሆነ መጥቀስ እሻለሁ። ወይንም፡ እኔ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በተለምዶ በሰላማዊ ትግል እየተባለ በሚጠራው ስልት የማምን ሆኜ አይደለም። የአገር ቤቱ ትግል ራሱን በቻለ ማእቀፍ ውስጥ ነው መቀመጥና መገምገም ያለበት ከሚል እንጂ። አሁንም ለማስተካከል ያህል አንዳቸው ስለአንዳቸው አይመለከታቸውም ወይንም አንዳቸው አንዳቸውን አያግዙም ለማለት ሳይሆን፡ ይሄ ይሁን ያኛው ግን አይሁን ስንል ሁለቱንም በየራሳቸው ተገቢ መሆን አለመሆን እንጂ፡ አንዳቸው ባንዳቸው ላይ ሊአመጡ ከሚችሉ ስሜት በመነጨ መሆን የለበትም ለማለት ነው። ምርጫ ውስጥ መግባት በምንም መልኩ ሌላኛውን ከምርጫ መለስ ያለ የትግል እንቅስቃሴ አያግድም። በሌላ የትግል መንገድ የምናምን ሰዎች በምንም መልኩ ምርጫ ውስጥ የሚገቡ ድርጅቶችን እንደ እንቅፋት ልንወስዳቸው አይገባም። ሌላኛውን የትግል ስልት መከተልና ምርጫ ውስጥ መግባት ከቶም መንገድ ላይ የማይጠላለፉና፡ ቢጠላለፉም እንኩዋን ሁለቱንም መንገዶች የሚከተሉትን ሰዎች የሚያጠቃ የጋራ ጠላት የጋራ ጨቋኝ ባለበት ሁኔታ፡ አንዱ ከሌላኛው ሳይቃረኑ የሚሄዱ ስልቶች ናቸው። ሌላ የትግል ስልት የሚከተሉ ሰዎች አገር ቤት ያሉትን ድርጅቶች እንደጠላት ወይም እንደምቀኛ ሊያዩ የሚችሉበት ምንም አይነት ምክንያታዊ ግንኙነት የለም።

ምርጫ ኢህአዴግን ለአለም ህብረተሰብ የማሳጣቱ አንደኛው መንገድ ነው። ኢህአዴግ ከዚህ በፊት ተሳጥቷል ትሉኝ ይሆናል። ግን ትግሉም ይሁን የማሳጣቱ ዘመቻ የሚያበቃው ያሸነፍን እለት ብቻ ነው። ዙምባቤንና ሱዳንን እንዲሁም ኬንያን ይመለከቷል። አምና አሳጥተነዋል። ካቻምናም አሳጥተነዋል። በቂ ነው የምንለው ደረጃ ላይ የምንደርሰው ግን የምንፈልገውን ያገኘን እለት ብቻ ናው። እስከዚያው ብዙ ስራ ይቀረናል ማለት ነው። አለም ኢህአዴግ ትልልቅ በደሎችን ቢፈጽምም፡ አብሮት ከመብላት ወደኋላ አላለም። ስለዚህ የማሳጣት ትግላችን ማባራት የለበትም ማለት ነው። ያ ደግሞ አንዱ መንገዱ ምርጫ መሳተፍና በራሱ በኢህአዴግ ሜዳ በኢህአዴግ መድረክ ኢህአዴግን ማሳጣት ነው ማለት ነው።

ምርጫ ውስጥ መግባት አለመግባት፡ ራሱ ምርጫ ነው። በምርጫ የምናምን ሰዎች፡ ተቃዋሚዎች ወደምርጫ ቢገቡ ምርጫቸውም ማክበር አለብን። የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫውን የማያምነበት ከሆነ፡ አያምንበትም ብዬ አምናለሁ፡ ያንን ሕዝቡ ለተቃዋሚዎች በተለያየ መንገድ ሊያሳያቸው ይችላል። ስለዚህ መራጩ ሕዝቡ ራሱ መልሱን ይስጣቸው እንጂ እኛ ወደ ማውገዝ ልንገባ አይገባም።

ተቃዋሚዎች አንሳተፍም ብለው ቢቀሩ እንኩዋን፡ ኢህአዴግ ሌሎች አሻንጉሊት ተቃዋሚዎችን ከመፍጠርና ምርጫው ውጤታማና ዴሞክራሲያዊ ነው ከማለት ወደኋላ አይልም። ይችልበታልም።

ወደ ምርጫው መግባት ማለት እስከምርጫው ዋዜማ ሀሳብን መለወጥ አይቻልም ማለት አይደለም። አገር ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚዎች ወደ ምርጫ ባይገቡ፡ አከተመላቸው። ወደምርጫ ቢገቡ ግን ኢህአዴግን ለመዋጋት ተጨማሪ እድል አገኙ ማለት ነው። እንደ ተወዳዳሪ ከምርጫ ቦርድም ይሁን ከውጭው አለም ታዛቢዎች ጋር መገናኘትና መነጋገር በየእለቱም ኢህአዴግን ማሳጣት ይችላሉ። ወደ ምርጫ ባይገቡ ወደምርጫ ቢገቡ የሚያገኙትን እድል አያገኙም። ተቃዋሚዎች ከምርጫ ውጪ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበት ምንም አጀንዳ የለም። ተቃዋሚ ድርጅቶች የጽዋ ማህበራት አይደሉም በየወሩ እየተሰበሰቡ፡ለመለያየት አይደለም የተደራጁት።

ወደ ምርጫ መግባት አንድ ትግል ስልት ነው እንጂ ብቸኛ ስልት አይደለም።

ወደምርጫ መግባት የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ አለ። በትክክል። ዋናው ጥያቄ ግን የቱ ይበልጣል ነው? ወደ ምርጫ በመግባታችን የሚመጣው ጥፋት ወይስ ባለመግባታችን የምናጣው እድል? ሁለተኛ ያ ወደ ምርጫ መግባት ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ተቃዋሚዎች በየደረጃው በሚወስዱት እርምጃ መቀነስ እንችላለን።

እጃቸውን አጣጥፈው ቢቀመጡ ምን እናገኛለን? ምክንያቱም በምርጫ በተገኘ አጋጣሚና ሰበብ ከመንቀሳቀስ ውጪ ተቃዋሚዎች ከምርጫ ውጪ ሊሰሩ የሚችሉት ነገር አይታየኝም። ተቃዋሚዎች የምርም ይሁን አይሁን፡ በኢህአዴግ ሕገ መንግስት እንወዳደራን ብለው ፈርመው ስርአቱ ባዘዘው ልክ ብቻ ለመንቀሳቀስ የተቋቋሙ ድርጅቶች ናቸው። ሰልፍና አመጽ፡ አድማና ሌላ ነገር፡ ሌላ ነግ ነው ተብለዋል። በዚያም ያለህጢያታቸው እስር ቤት ገብተዋል። ሌላ ነገር መደረግ አለበት ካልን፡ ያንን የምናደረግው ወይም ማድረግ ያለብን እኛ በዚህ የኢህአዴግ ሕገ መንግስት፡ አናምንም የምንልና በስርአቱ ላይ ያመጽን ሰወች እንጂ፡ አገር ቤት ያሉ ተቃዋሚዎች አይደሉም። እነሱማ መንገዳቸውን መርጠዋል፡ መንገዳቸውም ስርአቱ በፈቀደው ቦይ ውስጥ ብቻ የተወሰነ ነው። የ መንገድ ተሞክሮ ትንሽም ቢሆን ሰርቷል። ቀደም ሲልም ወደ ምርጫ ሲገባ፡ የተስተካከለ ነገር ኖሮ ሳይሆን፡ በዚያችው ኢህአዴግ በፈጠራት ክፍተት ውስጥ ለውጥ እናመጣለን ተብሎ ነው። ስለዚህ ከዚያ የተለየ ነገር የለም።

ሌላው ምክንያቴ፡ ሁሉንም እንቁላላችንን ባንድ ቅርጫት ማስቀመጥ የለብንም ከሚል የመነጨ ነው። በሌላ መንገድ የምንታገል በሌላ መንገድ መታገል እንችላለን። ትግሉን ሁሉ ግን ባንድ ስልት፡ ባንድ ድስት፡ ባንድ መንገድ ውስጥ ልናስገባው አንችልም። በምንም መልኩ አንድ መሆን አንችልም። ምክንያቱም ለዚህች አገር ያለን አጀንዳም አንድ አይደለምና። የአረናና የቅንጅት አጀንዳ፡ የኦነግና የኢህአፓ አጀንዳ፡ የኢዴአፓና የህብረት አጀንዳ አንድ አይደለም። ስለዚህ አንድ አይነት አቋም እንዲወስዱ መጠበቅ የለብንም። ያ ከሆነ፡ በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን ብለው አገር ቤት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች የመረጡት ስልትና አጀንዳ፡ ከነዚህ በብዛት ፈሰው ከሚገኙ አጀንዳዎች ውስጥ አንደ ነው። ያንን የነሱን ስልት ከኛ ስልት ጋር በግድ እንደብልቅህ ብንለው፡ የተለያየ ተፈጥሮና የተለያየ ንጥረ ነገር ስላላቸው፡ ዘይትና ውሀ የመደብለው ያህል ይሆናል ብቻ ሳይሆን፡ ሲሰበር ተሰበረ ነው።

ሰላማዊም እንበለው ሌላ ኢህአዴግ የሚፈቅደውን ብቻ መንገድ መከተል የራሱ ጉዳት የሉትም ማለት አይደለም። ጉዳት ይኖረዋል። ግን፡ በሰላማዊ ትግሉም ሰዎች መስዋእትነት ይከፍላሉ። ስለዚህ ብርቱካን ወይንም መራራ ወይንም ልደቱ ወይንም ኢንጂነር ሀይሉ በዚህ በመረጥኩት መንገድ ልሙት ካሉና ህዝብም ሊሞት ከተከተላቸው፡ ዜን ያ መብታቸው ነው ማለት ነው። በርግጥ ያንን መብታቸውን በቀጥታ የሚቃረን ያለ አይመስለኝም። ካለም ስህተት ነው። ነግር ግን ተቃርኖው የሚመጣው የነሱ የሰላማዊ ትግል ለምሳሌም በምርጫ መሳተፍ ኢህአዴግን ዴሞክራሲያዊ አስመስሎና በአለም ህብረተሰብ ዘንድ ዴሞክራሲ ያለ አስመስሎ ትርፉ ለኢህአዴግ ብቻ ነው። ያ ደግሞ ሌሎቻችን ኢህአዴግን ለመጣልም ይሁን ለማሳጣት በተለይም በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ዘንድ ጫና ለመፍጠር ለምናደርገው ትግል፡ እንቅፋት ይፈጥራል። አሉታዊም ነው ለሚለው ጥያቄ መልሱ ቀላል ባይሆንም፡ በተወሰነ መልኩ ያንን ስጋት መቅረፍ ይቻላል። ተቃዋሚዎች በአገር ቤት ተመዝግበን መንቀሳቀስ የምንችልበት ክፍተት አለ፡ በዚያም ተንቀሳቅሰን፡ በምርጫ በመሳተፍ ውጤት እናመጣለን ብለው በመሰናዳት፡ ነገር ግን በምርጫው መሳተፍ ኢህአዴግን ከመጥቀም ውጪ እርባና ቢስና ትርጉም የለሽ መሆኑነ አረጋግጠው ከምርጫም ይሁን ከሌሎች መሰል እንቅስቃሴዎች ራሳቸውን ማግለልና እኛ ኢህአዴግን በአለም ማህበረሰብ ፊት ማሳጣት የፈለግንበትን ጫና መፍጠር ይችላሉ። ስለዚህም ወደምርጫ መግባት አስፈላጊ ነው ብቻ ሳይሆን የግድ ነው።

እንደማሰሪያም፡ ለኔ መጥፎው ተቃዋሚዎች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ ምርጫ መግባታቸው ሳይሆን፡ ምርጫው ምርጫ እንደማይሆን እያወቁ፡ በምርጫው ውስጥ ቢቆዩና የኢህአዴግ አዳማቂ ቢሆኑ ነው። ምርጫን ምርጫ የሚያሰኘው፡ ድምጽ የሚሰጥበት እለት የሚደረግ ሽርጉድ አይደለም። በሌላ አነጋገር፡ ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ ሂደት ውስጥ ተቃዋሚዎች አሸነፉ ቢባልም ምርጫውን ዴሞክራሲያዊ አያደርገውም። ስለዚህ ተቃዋሚዎች ወደ ምርጫ ገብተው ሲንቀሳቀሱ በሚያልፉበት ሂደት ውስጥ በሚያጋጥሚቸው፡ አግባብ ያልሆኑ ድርጊቶች ኢህአዴግን ካሳጡና፡ የምትገኘውን ትንሽ መድረክ ተጠቅመው ከላይ የዘረዘርኳቸውን ድሎች ካስመዘገቡ በኋላ፡ የኢህአዴግን የምርጫ ውጤት ህጋዊ ለማስመሰል ብቻ ያህል ወይንም ከዚያ የበለጠ ፋይዳ በማይኖረው ሁኔታ ምርጫ ውስጥ ቢቆዩ፡ ለኔ ትልቁ ችግር ያ ነው። ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ በፈቀደላቸው ልክ ብቻ ነው ወይ መንቀሳቀስ ያለባቸው፡ ከዚያ ባሻገር ትግላቸውን ማሳደግ የለባቸውም ወይ፡ ይሄ መልሱ ግልጽ ነው። እነሱ ናቸው የሚያውቁት። አመሰግናለሁ።